# ጀግና እንደ ብርሌ

አብርሃም በየነ

(ለጓድ ጳውሎስ የተገጠመ)

ሰው በሰውነቱ ስብዕና ተላብሶ

በጠጣር ዕምነቱ ዕውነትን አንግሶ

ባመለካከቱ ተችሮት ዕውቅና

ካገር እንዲጠፉ አድሎና ጭቆና

ህዝብ እንዳይበደል ፍትህ አዘንብሎ

ስርዓቱን ሊጥል ሳያሰልስ ታግሎ

ለህዝብ እንጂ ላገር ለራሱ ያልኖረ

እንደ ሰው ተሸኘ ሞተ ተቀበረ።

እንደ ጓድ ጳውሎስ ሳሉ በቁመና

ከፍትህ ተጣብቶ ለሰው ስብዕና

ራስን ካልሰጡ ለህይዎት ሳይሳሱ

እንደ ሰው ተሰርተው እንደ ሰው ቢፈርሱ

ምኑም ሰው አያደርግ ሰው መሆን በራሱ።

ሰው በሰውነቱ እንዲታወቅ ገዝፎ

ብሩህ ቀን ለማምጣት ራሱን ሰይፎ

ሲታገል ለኖረ የፍትህ ከንዋታ

ዕርግማን መሰለኝ አፈር ላይ ምኝታ።

የድሆችን በራፍ ዘግቶ በጭራሮ

አንጀታቸው ሲርቅ በራብ ተጨማትሮ

ደልቶት ተዘባኖ ብዙ ሀብት አካብቶ

ሌላው በድህነት ሲኖር ተቆራምቶ

ተበደልኩ እንዳይል አንደበቱን ዘግቶ

እንደ ጨው አሟሙቶ እንደ ሰም አቅልጦ

እረግጦ የገዛም የሰው ሙብት ድጦ

በሰው አምሳል ቆሞ እንደ ሰው ሲጠራ

ሁሉም ሰው ነኝ ይላል በስውነት ተራ።

ኧረ እናንተ ሆየ ለሰሚው ነው ግራ

ጅግናም እንደ በርጌስ በሰውነት ተራ

በሞት ድርን ገብቶ ስራው ሳይሰፈር

ድንገት ጊዜው ሲመሽ ይበላዋል አፈር።

ጳውሎስ ያንተም ህይዎት ጌዜው ስለመሼ

በሀዘን ልሸኝህ እምባየን አፍስሼ።

መስከረም 2007